# የካቲት የኢትዮጵያ ሕዝብ የድል ቀን

የኢትዮጵያ ሕዝብ በፋሽስቱ የኢጣሊያን ጦር ላይ በአድዋ የተቀዳጀው ታሪካዊ ድል በእርግጥም ለመላው ጥቁር ሕዝብ አርአያ የሆነና በፀረ ቅኝ ግዛት ትግል ታሪክ ወስጥ አኩሪ ምዕራፍን የያዘ ነው። ኢትዮጵያ ለዘመናት የቆየ ታሪክ ያላት ሉዓላዊ ሀገር መሆኑዋንም በአድዋ ድል አረጋግጣለች።

የአድዋ ድል የእብሪተኞች ሽንፈት ነው። ሞሶሎኒ በእብሪት፤ በጉልበቱና በዘመናዊ መሳሪያው ተማምኖ ንቀት የነበረውን ጥቁር ሕዝብ አንበርክኮ ለመቅጣት አስቦ ድንበር ጥሶ ሲገባ  በገጠመው የማይበገር ኃይል ሽንፈትንና ውርደትን መከናነቡ ነፃነታቸውንና ክብራቸውን ከምንም በላይ የሚወዱ እና ለምንም ዓይነት ምድራዊ ኃይል የማይንበረከኩ ኢትዮጵያዊያንን ማንነት እንዲያውቅ አድርጎታል። አፍሪካን በቅኝ ግዛት የተቀራመቱት አውሮፓዊያንም እንዲሁ ይዘውት የቆዩት ዘረኛ የበላይነት ስሜት ከንቱ ቅዠት ሆኖ እንዲቀር አድርጎታል። በአንፃሩ የአድዋ ድል ለመጪዎቹ የአፍሪካ የነፃነት ታጋዮች ታላቅ አርአያቸው ለመሆኑ የጋናው ኩዋሚ ንክሩማህ፣ የኬኒያው ጆሞ ኬኒያታ፣ የናይጀሪያው ኒማድ አዝካዌ እና ሌሎችም ታላላቅ አፍሪካዊያን የነፃነት ታጋዮች ደጋግመው በኩራት መስክረዋል።

ዛሬ ኢትዮጵያን አዋርደው ዜጎቿን  ሁሉ አንገት ሊያሰበሩና ሊያሳፍሩ የሚጥሩት አገር በቀል እንክርዳዶች የአድዋን ድል(ቅርስ) ማፈራረስና በተለይም ወጣቱን ትውልድ የአድዋ ድል ታሪክ ወራሽ እንዳይሆን፣ ለአገር ሉዓላዊነትና ለሕዝብ መብት እንዳይቆም የትግል ወኔውን ሊሰልቡት ሲጥሩ ይታያል። ለዚህ ጥረታቸው መጠቀሚያ ይሆን ዘንድ ወጣቱን ትውልድ በጎጥና በሃይማኖት በመከፋፈል በኢትዮጵያዊነቱ እንዳይኮራና በማንነቱ እንዳይመካ፣ ለአምባገንኖችና ለባእዳን እንደያጎነብስ ለማድረግ ደፋ ቀና እያሉ ነው። ይህ በብሔራዊ ህልውና ላይ የተከፈተ ጦርነት ካነጣጠረባቸው አብይ ጉዳዮች መካከል ወጣቱን ትውልድ አያት ቅድመ አያቱ ካቆዩለት አኩሪ ቅርስ መነጠል አንዱ ስለሆነ፣ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ማንሳት የግድ ይሆንል፤ ወጣቱ ትውልድ አድዋን እንዴት ይመለከተዋል? አያት ቅድመ አያቶቹ ያቆዩለትን ታሪካዊ ቅርስ እየጠበቀ ነው ወይ? ለሚሉትና መሰል መሠረታዊ ጥያቄዎች መልስ በቅድሚያ መሻት ትውልዱን ከታሪካዊ ማንነቱ ማዛመዱ ብቻ ሳይሆን የአገር ማዳኑም ተጋድሎ መሠረቱ እንዲጠነክርና በጠላት ወከባ አቅጣጫውን እንዳይስት ያደርጋል ።

አድዋ የሀቀኛ አገር ወዳድነት ትርጉም መገለጫ ነው። ከምንም በላይ ሀገርን  ማስቀድም፣ ለሀገርና ለሰንደቅ ዓላማ ክብር፣ ለነፃነት መታገልና መስዋዕት መሆን ማለት ነው። አድዋ የኢትዮጵያዊነት ምሳሌ ነው። ዘር፣ ጎሳ፣ ሃይማኖትና ጾታ ሳይለይ በሀገራዊ ስሜት ለውድ ሀገር መሰለፍን፣ ከፍፍልና ቅጥረኝነትን አስወግዶ ለኢትዮጵያ መታገልን ያስተማረ አኩሪ ታሪክ ነው።

‘የሀበሻ ጀብዱ’ በሚለው መፅሀፉ፣ አዶልፍ ፓርላሳክ፣ በማይጨው ጦርነት አብሮ በመዝመቱ የኢትዮጵያዊያን አርበኞች ቆራጥነትና አይበገሬነት በምሳሌ ሲገልፅ ስለ አንድ አባት አርበኛ እንዲህ ይላል፡- “ደጃዝማች አስፋው አንድ አይና ናቸው። ሁለተኛውን አይናቸውን በታላቁና ገናናው የአድዋ ድል ከእምዬ ምኒልክ ጋር ሲወጉ አጥተዋል። አንድ የጣሊያን መኮንን በፈረስ ሆኖ የተኮሳት ጥይት አይናቸውን ብታፈሰውም፣ ያ ሳይበግራቸው ዘለው በጎራዴ የዝያን ጣልያን አንገት ቀልተዋል። አዎ! ደጃዝማች ከዚያች ቀን ጀምሮ አንድ አይናቸው ለዘላለሙ ብትጨልምም፣ ዛሬም በአንድ ዓይናቸው በዚያው ጎራዴ፣ በዚያችው መንገድ፣ ከተመሳሳይ ጠላት ጋር ለመግጠም እነሆ ጦራቸውን ይዘው ራስ ካሳን ተከትለው እዚች ደርሰዋል።” በሚል ያለውን ታላቅ አድናቀት በምሳሌ ይገልፃል።

አድዋ ከትውልድ ትውልድ ሲዘከር የሚኖር አኩሪ ቅርሳችን ነው። በተለይ አሁን አገራችን ከምትገኝበት አደገኛ ሁኔታ አንፃር ለአሁኑ ትውልድ ወጣቶች ታላቅ ምሳሌ የሚሆንና ከቶም ልንዘነጋው የማይገባ በየዓመቱ  በታላቅ ድምቀት ልንዘክረውና ልናከብረው የሚገባ ታሪክ ነው።

ከሕዝብ ጎን በመሰለፍ የሚከተሉት እምንት ሳያግዳቸው ለአገራቸው ክብር ሕዝቡን በመቀስቀስና በማስተባበር በጦርነቱም በመሳተፍ አረአያነታቸውን ያልነፈጉት የክርስትናም ሆነ የእስልምና ሃይማኖት አባት መሪዎች የሕዝቡን ሞራል ከእለት እለት ከፍ እንዲል በማድረጉ ረገድ ከፍተኛ ድርሻ አበርክተዋል። ለነጻነት በተደረገው ፍልሚያ ውድ ህይወታቸውን አሳልፈው ሰጥተዋል። ከነዚህ በርካታ ታላቅ መንፈሳዊ አባቶች ውስጥ አቡነ- ጴጥሮስ አንዱ ናቸው ።

አኩሪነቱም ለኢትዮጵያ ሕዝብ ብቻ ሳይሆን ለመላው የጥቁር ሕዝብ ጭምር ነው።

በባዶ እግሩ የሚሄድ ሁዋላ ቀር ሀይል አለ ከተባለ ዘመናዊ መሳሪያን ከታጠቀ የጣሊያን ጦር ጋር ውጊያ መግጠም እብደት ነው ብለው ምዕራባዊያን ጋዜጦች ተሳልቀው እንደነበር ሳንዘነጋ ፣ እኛም የትውልድን ወኔ በመግደል አገር ለማፈራረስ የተነሳው የቅርብና የሩቅ ጠላት አቅመ ቢሶች ሊያደርገን ቢባትልም ልክ እንዳባቶቻችን ዳግም የሀፍረት ማቁን ልናለብሰው መነሳት አለብን።

እኛ የኢወክንድ አባላት የአድዋን ድል ፲፱ኛ ዓመት ስንዘክር ሀገራችን ኢትዮጵያ ከዚያን ወቅት ባላነስ አደጋ ውስጥ ገብታ ህልውናዋ ለፈተና የተዳረገ መሆኑን እንገነዛባልን። እናት አገራችንን ከተጋረጠባት አደጋ ለማዳን ከአድዋው ጊዜ የበለጠ መነሳሳትና መታገል እንደሚጠበቅብን እየተረዳን ሀገር ወዳዱ ሁሉ በአገር አድን ትግሉ ውስጥ እንዲሳተፍ ጥሪ እናደርጋለን።

ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኖራለች!